# የተማሪ መረጃ መልቀቂያ ፈቃድ መጠየቂያ

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ:

እኔ በዚህ የትምህርት አመት መምህራን በማስተማር የተዋጣላቸው ባለሙያ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚደረግ ምዘና ላይ ተሳታፊ ነኝ። በሙያዊ የትምህርት አሰጣጥ መስፈርቶች ብሔራዊ ቦርድ (**ብሔራዊ ቦርዱ**) እየተካሄደ በሚገኘው በዚህ ምዘና ውስጥ ያለኝ ተሳትፎ በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው። የዚህ ምዘና ዋና ዋና ዓላማዎች አንድ አስተማሪ ከአንድ የተዋጣለት መምህር የሚጠበቅ ዕውቀት እና የተግባር ክህሎቶችን ስለማሳየቱ፣ ለተማሪዎች የትምህርት አሰጣጥን የሚያሻሽል እንዲሁም በማስተማር ላይ የላቀ ብቃትን የሚያበረታታ ስለመሆኑ ውሳኔዎችን መስጠት ናቸው።

ይህ ምዘና በልጅዎ መማሪያ ክፍል ውስጥ እየተሰጡ ያሉ ትምህርቶችን አጫጭር የድምጽ እና ምስል ቅጂዎች እና/ወይም ፎቶግራፎች አዘጋጅቶ ማስረከብን ይጠይቃል። ምንም እንኳን ቀረጻዎቹ/ፎቶግራፎቹ ተማሪዎችን የሚያሳዩ ወይም የሚያሳትፉ ቢሆኑም፣ ዋናው ትኩረቱ በትምህርቱ ላይ እንጂ በተማሪዎቹ ላይ አይደለም። በዚህ ምዘና ወቅት፣ የልጅዎ ምስል እና ድምጽ በቪዲዮው ላይ ሊቀረጽ እንዲሁም ፎቶግራፍ ሊነሳ ይችላል፣ከዚያም ቀረጻዎቹ/ፎቶግራፎቹ ለብሔራዊ ቦርድ ይላካሉ። የማቀርባቸው የምዘና ግኝቶች (**የምዘናው ግኝቶች**) የጽሑፍ አስተያየቶቼን፣ የማስተማሪያ ይዘቶች፣ ድርሰቶች፣ የመማሪያ ክፍል እቅዶች፣ ለተማሪዎች የተመደቡ ስራዎች እና አስተያየቶችንም እንዲሁ ያካትታሉ።

በተጨማሪም፣ እንደ ምዘናው አንድ አካል፣ የማስተማር ልምዶቼን ለማሳየት የልጅዎን ስራ ሊያካትት የሚችል የተማሪ ስራ ናሙናዎችን (**የተማሪ ስራዎች**) እንዳቀርብ ልጠየቅ እችላለሁ። እንደ ምዘናው አንድ አካል የማቀርባቸው ይዘቶች ወይም ቀረጻዎች ላይ የማንኛውም ተማሪ ስም አይካተትም።

ብሔራዊ ቦርዱ የማቀርባቸውን ግኝቶች የመጠቀም ሁሉን አቀፍ መብቶች ያሉት ሲሆን በማቀርባቸው ግኝቶች ውስጥ የነበሩኝን እና ለማቀርባቸው ግኝቶች ያሉኝን ሁሉንም መብቶቼን ለብሔራዊ ቦርዱ አስተላልፋለሁ። ብሔራዊ ቦርዱ የማቀርበውን የተማሪ ስራ በተመለከተ እንዲሁ የተወሰኑ መብቶች ይኖሩታል። ብሔራዊ ቦርዱ በትምህርት እና በማስተማር ላይ የላቀ ብቃት የማስተዋወቅ ተልእኮውን የበለጠ ለማሳደግ ያቀረብኳቸውን ግኝቶች እና የተማሪ ስራዎች ሊጠቀም ይችላል። በየትኛውም ሁኔታ ብሔራዊ ቦርዱ የሚስጢራዊነት መመሪያውን ያከብራል፣ ይህም በብሔራዊ ቦርድ የምስክር ወረቀት መመሪያ[http://www.nbpts.org/wp-content/uploads/Guide_to_NB_Certification.pdf](http://www.nbpts.org/wp-content/uploads/Guide_to_NB_Certification.pdf).ውስጥ ይገኛል። ለምሳሌ፣ የማስረክባቸው ግኝቶች እኔ ከማካሂደው የብሔራዊ ቦርድ ምዘና እና በምዘናው ሂደት ውስጥ ከሚረዱ ሶስተኛ ወገኖች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ብሔራዊ ቦርዱ በብሔራዊ ቦርድ የስራ ውጤቶች እና ህትመቶች ውስጥ ግኝቶቼን እና የተማሪዎችን ስራ ሊጠቀም ይችላል። ብሔራዊ ቦርዱ ግኝቶቼን እና የተማሪ ስራዎችን ATLAS ተብሎ በሚጠራ በይለፍ ቃል በተጠበቀ የኦንላይን የመረጃ ቋት ውስጥ ለማስገባት ከእኔ የተለየ ፈቃድ ሊፈልግ ይችላል፣ይህም ለትምህርት፣ ለጥናታዊ ምርምር እና ለሙያዊ እድገት አላማ ሌሎች ሊያገኟቸው የሚችሉበት ሰፍራ ነው። የሚቀርቡ ግኝቶች ወደ ATLAS የሚገቡት ከእኔ የተለየ የATLAS ፈቃድ እና የመልቀቂያ ቅጽ ከተገኘ በኋላ ብቻ ነው። በ ATLAS የኦንላይን የመረጃ ቋት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ደንቦች እና ሁኔታዎችን እዚህ ላይ መመልከት ይችላሉ:- [https://atlas.nbpts.org/terms](https://atlas.nbpts.org/terms). ብሔራዊ ቦርዱ ለግኝቶቹ እና ለተማሪ የስራ ውጤቶች መዳረሻ ከሚሰጣቸው ሰዎች ክፍያዎችን ሊቀበል ይችላል። እነዚህ ትግበረዎች የእኔ ግኝቶች እና የተማሪ የስራ ውጤቶች በተለያዩ ግለሰቦች፣ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች እንዲታዩ ሊያደርጉ ይችላሉ። በድጋሚ፣ ሆኖም፣ የልጅዎ ስም በግኝቶቹ ወይም በተማሪው ስራ ውስጥ አይገለጽም።

በዚህ ደብዳቤ እና በተያያዘው የተማሪ መረጃ መልቀቂያ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ መሠረት ብቻ በብሔራዊ ቦርዱ ጥቅም ላይ እንዲውልና እንዲገለጽ የልጅዎን ድምጽ ወይም ምስል የሚያካትቱ ቀረጻዎችን እና ፎቶግራፎችን ለብሔራዊ ቦርዱ እንዳቀርብ ፈቃድዎን ለመጠየቅ እየጻፍኩ ነው። ፈቃድ ሲሰጡ፣ የግምገማዬ አካል አድርጌ የማቀርበውን ማንኛውንም የልጅዎን የተማሪ ስራ እንዲጠቀም እንዲሁም ከየትኛውም የተማሪ ስራዎች ጋር የተያያዙ የቅጂ መብቶች፣ የማስታወቂያ መብቶች እና ሌሎች መብቶች እንዲኖረው እና እንዲጠቀም ለብሔራዊ ቦርዱ ዘላቂ፣ የማይሻር እና ከክፍያ ነጻ ፈቃድ እየሰጡ ሲሆን ከግኝቶቹ ወይም ከተማሪ የስራ ውጤቶች አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከሁሉም የይገባኛል ጥያቄዎች (የግላዊ መረጃ ጥሰትን ጨምሮ) ብሔራዊ ቦርዱን ነጻ እያደረጉ ነው።

በልጅዎ ከላይ በተዘረዘሩት ተግባራት ውስጥ የመሳተፍ እና በብሔራዊ ቦርዱ ግኝቶቹን እና የተማሪ ስራዎችን በዚህ ደብዳቤ በተገለጸው መንገድ የመጠቀም መብት ከተስማሙ፣ እባክዎን የተያያዘውን የተማሪ መረጃ መልቀቂያ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ይፈርሙ (**<u>እንዲሁም</u>** ልጅዎ 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ)እንዲፈርም ያድርጉ)። ይህ የእርሰዎን ፈቃድ የሚገልጸውን ቅጽ የማሰቀምጠው ሲሆን ብሔራዊ ቦርዱ በጠየቀበት ጊዜ ላቀርበው እችላለሁ። በልጅዎ ተሳትፎ ካልተስማሙ፣ ቀረጻዎች ሲካሄዱ እና ፎቶግራፎች ሲወሰዱ ልጅዎ ከእይታ ውጭ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን በማቀርባቸው የተማሪዎች ስራ ውስጥ የልጅዎን ስራ አላካተትም።

በጣም አመሰግናለሁ።

ከሰላምታ ጋር፣

(የእጩ ፊርማ)

© 2021 የሙያዊ የትምህርት አሰጣጥ መስፈርቶች ብሔራዊ ቦርድ | መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# የተማሪ መረጃ መልቀቂያ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ

(በማንኛውም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ተማሪ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ
**እንዲሁም** ዕድሜያቸው 18 ወይም ከዚያ በላይ በሆናቸው እና በዚህ ምዘና ውስጥ በተሳተፉ ተማሪዎች በሙሉ) መሞላት አለበት)

የተማሪ ስም: ______________________________

የትምህርት ቤት ስም እና የአስተማሪ ስም:______________________________

አድራሻዋ:______________________________

*ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ*

እኔ ከላይ የተጠቀሰው **ልጅ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ** ነኝ። በሙያዊ የትምህርት አሰጣጥ መስፈርቶች ብሔራዊ ቦርድ (ብሔራዊ ቦርድ) እየተካሄደ ያለውን የመምህራን ምዘና በተመለከተ ከዚህ ቅጽ (ደብዳቤው) ጋር የተያያዘውን ደብዳቤ ተቀብዬ ያነበብኩ ሲሆን በሚከተለው ተሰማምቻለው:

☐ ለመምህሩ (እርሰዎ) እና ከላይ ለተጠቀሰው ትምህርት ቤት የልጄን ምስል እና ድምጽ በቪዲዮ እንድትቀርጹ እንዲሁም ልጄ በ ____________________(የትምህርት ቤት ስም) በ ______________________(የአስተማሪ ስም) በሚመራ ክፍል ውስጥ ሲሳተፍ ፎቶግራፎችን እንድታነሱ እንዲሁም የእነዚህን ቀረጻዎች እና ፎቶግራፎች ቅጂዎች ለብሔራዊ ቦርድ እንድትሰጡ **ፈቃድ ሰጥቻለው**፤ እንዲሁም ልጄ ያዘጋጀቸውን ይዘቶች ወይም በክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ሊያዘጋጃቸው የሚችላቸውን ስራዎች ቅጂዎች ለብሔራዊ ቦርዱ እንድታቀርቡ ለእርሰዎ እና ትምህርት ቤቱ ፈቃድ ሰጥቻችኋለሁ፣ ሁሉም ከዚህ በታች በተገለጹት ደንቦች እና ሁኔታዎች መሠረት ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው:

1. የልጄ ስም ለብሔራዊ ቦርዱ በሚቀርቡ ቀረጻዎች፣ ፎቶግራፎች ወይም የትምህርት ቤት ስራዎች ላይ አይታይም።
2. ብሔራዊ ቦርዱ፣ እርሰዎ ለብሔራዊ ቦርዱ የሚያቀርቧቸውን ይዘቶች እዚህ ላይ እና በደብዳቤው ላይ ለተገለጹት ዓላማዎች ብቻ ሊጠቀምባቸው ይችላል።
3. ለብሔራዊ ቦርዱ የሚያቀርቧቸውን ይዘቶች ቅጂ ብሔራዊ ቦርዱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይፋ ሊያወጣ ይችላል: (ሀ) ATLAS database (አትላስ ዳታቤዝ) በመባል የሚታወቅ፣ ለትምህርታዊ፣ ለጥናታዊ ምርምር ወይም ለሙያዊ እድገት ዓላማዎች የሚውል፣ በይለፍ ቃል የተጠበቀ የብሔራዊ ቦርድ የመረጃ ቋትን ለሚጠቀሙ ግለሰቦች፣ እና (ለ) እንደዚህ ያሉ ይዘቶች ሊካተቱ በሚችሉበት የብሔራዊ ቦርድ የስራ ውጤቶች ወይም ህትመቶች ውስጥ።

☐ የልጄን ምስል ወይም ድምጽ እንድትቀርጹ ወይም በመማሪያ ክፍል ተግባራት ወቅት በልጄ የተሰሩ ስራዎችን እንድትቀዱ ወይም ለብሔራዊ ቦርድ እንድታጋሩ ለእርሰዎም ሆነ ለትምህርት ቤቱ **ፈቃድ አልሰጥም**።

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:______________________________ቀን:______________

*አዋቂ ተማሪ*

እኔ ስሜ ከላይ የተጠቀሰው ተማሪ ሰሆን 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ ነኝ። በሙያዊ የትምህርት አሰጣጥ መስፈርቶች ብሔራዊ ቦርድ (ብሔራዊ ቦርድ) እየተካሄደ ያለውን የመምህራን ምዘና በተመለከተ ከዚህ ቅጽ (ደብዳቤው) ጋር የተያያዘውን ደብዳቤ ያነበብኩ ሲሆን በሚከተለው ተሰማምቻለው:

☐ ለመምህሩ (እርሰዎ) እና ከላይ ለተጠቀሰው ትምህርት ቤት የእኔን ምስል እና ድምጽ በቪዲዮ እንድትቀርጹ እንዲሁም በ (የትምህርት ቤት ስም) በ (የአስተማሪ ስም) በሚመራ ክፍል ውስጥ ሰሳተፍ ፎቶግራፎችን እንድታነሱ እንዲሁም የእነዚህን ቀረጻዎች እና ፎቶግራፎች ቅጂዎች ለብሔራዊ ቦርድ እንድትሰጡ **ፈቃድ ሰጥቻለው**፤ እንዲሁም ያዘጋጀኋቸውን ወይም በክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ላዘጋጃቸው የምችላቸውን ስራዎች ቅጂዎች ለብሔራዊ ቦርዱ እንድታቀርቡ ለእርሰዎ እና ትምህርት ቤቱ ፈቃድ ሰጥቻችኋለሁ፣ ሁሉም ከዚህ በታች በተገለጹት ደንቦች እና ሁኔታዎች መሠረት ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው:

4. ሰሜ ለብሔራዊ ቦርዱ በሚቀርቡ ቀረጻዎች፣ ፎቶግራፎች ወይም የትምህርት ቤት ስራዎች ላይ አይታይም።
5. ብሔራዊ ቦርዱ፣ እርሰዎ ለብሔራዊ ቦርዱ የሚያቀርቧቸውን ይዘቶች እዚህ ላይ እና በደብዳቤው ላይ ለተገለጹት ዓላማዎች ብቻ ሊጠቀምባቸው ይችላል።
6. ለብሔራዊ ቦርዱ የሚያቀርቧቸውን ይዘቶች ቅጂ ብሔራዊ ቦርዱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይፋ ሊያወጣ ይችላል: (ሀ) ATLAS database (አትላስ ዳታቤዝ) በመባል የሚታወቅ፣ ለትምህርታዊ፣ ለጥናታዊ ምርምር ወይም ለሙያዊ እድገት ዓላማዎች የሚውል፣ በይለፍ ቃል የተጠበቀ የብሔራዊ ቦርድ የመረጃ ቋትን ለሚጠቀሙ ግለሰቦች፣ እና (ለ) እንደዚህ ያሉ ይዘቶች ሊካተቱ በሚችሉበት የብሔራዊ ቦርድ የስራ ውጤቶች ወይም ህትመቶች ውስጥ።

☐ የእኔን ምስል ወይም ድምጽ እንድትቀርጹ ወይም በመማሪያ ክፍል ተግባራት ወቅት የምሰራቸውን ስራዎች እንድትቀዱ ወይም ለብሔራዊ ቦርድ እንድታጋሩ ለእርሰዎም ሆነ ለትምህርት ቤቱ **ፈቃድ አልሰጥም**።

የተማሪ ፊርማ:______________________________ቀን:______________

የትውልድ ቀን:____________________

© 2021 የሙያዊ የትምህርት አሰጣጥ መስፈርቶች ብሔራዊ ቦርድ | መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።